በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና በንግድ ባንክ ወኪል ቅርንጫፎች በኩል የሚገዛው ወርቅ የሚመራበት የሥራ ሂደት (መመሪያ ቁጥር 312/2013)

Gold Purchased Through the Branches of the National Bank of Ethiopia and Commercial Bank Agents (Directive No. 312/2013)

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
National Bank of Ethiopia

ጥር 25፥ 2013

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

ADDIS ABABA

<u>በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና በንግድ ባንክ ወኪል ቅርንጫፎች በኩል የሚገዛው ወርቅ የሚመራበት የሥራ ሂደት መመሪያ ቁጥር 312/2013</u>

1. ማብያ

1.1 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የውጭ ምንዛሪ ያስተዳድራል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባንኩ የውጭ ምንዛሪ አቅምን ለማጎልበት የሚረዱ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ ወርቅ የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ አንዱ ሀብት እንደመሆኑ መጠን ከአገር ውስጥ አቅራቢ ደርጅቶች በመግዛት እና ወደ ውጭ አጓጉዞ በመሸጥ ወይም በውጭ ባንኮች (Correspondent banks) ውስጥ አስቀምጦ በማስደር ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ክምችት ወይም ግኝት አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ባንኩ ባለፉት ዓመታት ሰፊ ጥረት አደርጓል፡፡ አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

1.2 ይሁንና በሀገሪቱ በተለምዶአዊ አሠራር ወርቅ የሚያመርቱ ማህበራት/ግለሰብ ነጋዴዎች በርካታ ቢሆኑም ሁሉም የሚያመርቱትን ወርቅ ሕጋዊ በሆነ መልክ ለባንኩ አቅርበው አይሸጡም፡ በባህላዊ የወርቅ ምርት በሚሳተዋሉ በርካታ ችግሮች ምክንያት ከዘርፉ ማግኘት የነበረበት የውጭ ምንዛሪ እና ሌሎች ልዩ ልዩ ገቢዎች ከሚጠበቀው በታች እየወረዱ በመምጣታቸው እንደአገር የሚጠበቀውን ውጤት ማግኘት አልተቻለም፡ ከሌሎች ችግሮች በተጨማሪ ለአቅራቢዎች የሚፈለው ማበረታቻ ተወዳዳሪ ባለመሆኑ ለባንኩ መቅረብ የነበረበት ወርቅ በሕገወጥ መንገድ በኮንትሮባንድ ገበያ እንዲሸጥ አንዱ ምክያት መሆኑ በተደረገው ጥናት ተረጋግጧል፡፡

1.3 ከዚህ ዘርፍ የሚገኘው ሐብት በአግባቡ ለአገር ጥቅም ለማዋል እና አምራች ደርጅቶች ሕጋዊ በሆነ አካሄድ እንዲበረታቱ ለማድረግ የወርቅ ሽያጭ እና ክፍያ አፈጻጸም በአግባቡ የሚመራበት ደንብ ቁጥር GT/001/2008 ቀደም ሲል በባንኩ ተሻሽሎ በሥራ ላይ ውሏል፡፡ በዚሁ ደንብ መሠረት አምራች ማህበራት እና ግለሰብ ነጋዴዎች ወርቅ ለባንኩ በመቅረብ ላይ ይገኛሉ፡ የወርቅ አቅርቦት በማሻሻል ከባህላዊ የወርቅ ዘርፍ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ማሳደግ እንዲቻል መግስት አቅራቢዎችን በማበረታታት ከዘርፉ ማግኘት የሚገባውን አገራዊ ጠቀሜታ ለማሳደግ ወስኗል፡፡

1.4 በመሆኑም፣ ከላይ በተራ ቁጥር (1.3) የተጠቀሰውን ለማተግበር በማዕከልም ሆነ በወኪልና የወርቅ ግዥ የሚከናወኑ የንግድ ባንክ ቅርንጫፎችም ሆኑ ብሔራዊ ባንክ የሚመራበትን አዲስ የማበረታቻ ዋጋን ጨምሮ የወርቅ ግዥ የሥራ ሂደት አፈጻጸም፣ ክምችት እና ርክክብ አፈጻጸም የሥራ ሂደት **(Procedure Manual)** እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

2. የሰነዱ ጠቀሜታ እና ዓላማ

2.1 መንግሥት የውጭ ምንዛሪ ሊያስገኙ የሚችሉ የኢኮኖሚ ዘርፎችን ለማጠናከር በነደፈው ስትራቴጂ መሠረት በጥቃቅን የወርቅ ምርት ሥራ ላይ የተሰማሩ ግለሰብ ነጋዴዎች እና ማኅበራት ያመረቱትን ምርት ሕጋዊ በሆነ መልክ ወደ ብሔራዊ ባንክ የወርቅ ግዥ ማዕከል እና ተመረጡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች እንዲያቀርቡ እና ክፍያቸውን በወቅቱ እንዲያገኙ የሚያስችል ነው፡

2.2 ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ያስችላል፡፡

2.3 የሥራ ሂደት **(Procedure Manual)** ማኖር ሥራውን ለመቆጣጠርና ለመከታተል አመቺ በመሆኑ ሥራውን በተገቢው ሁኔታ ለማከናወን ያግዛል፡፡

3. ወርቅ ለማቅረብ መሟላት የሚገባቸው ሰነዶች/መረጃዎች

ማንኛውም ነጋዴ ወርቅ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለማቅረብ በቅድሚያ ቀጥሎ የተጠቀሱትን ሰነዶች ማቅረብ አለበት፡፡

3.1 ከክልል ቢሮ ወይም ከማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት ወይም ከሚመለከታቸው ማዕቤቶች የተሰጠ የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣

3.2 በዓመት አንድ ጊዜ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ/የማኅበር ቤት መታወቂያ፣

3.3 ማህበር ከሆነ የመመሥረቻ ጽሑፍ፣ /ሚያገግጫ ከወልና ማስረጃ/ ፣

3.4 የማህበሩ ማኅደረያ ደንብ፣

3.5 ወርቅ ለባንኩ ለማቅረብ የመጣው ሰው ከማህበሩ የውክልና ደብዳቤ የያዘ ወይም የማህበሩ ሊቀመንበር መሆኑን የሚገልጽ መታወቂያ፣

3.6 የወርቅ አቅራቢው ማህበር ሊቀመንበር ወይም ግለሰብ 2 ጉርድ ፎቶግራፍ እና

3.7 የአምራቾች የሥራ ፈቃድ፣ ከላይ የተጠቀሰት ሰነዶችና ማስረጃዎች ከዋናው ጋር ከተመሳከሩ በኋላ አንድ አንድ ኮፒ በስማቸው ፋይል ተከፍቶ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

4. የወርቅ ግዥ አፈጻጸም የሥራ ሂደት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማዕከላዊ የወርቅ ግዥ ቢሮ እና ክልል የሚኙ የተመረጡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወርቅ ግዥ ቅርንጫፎች ከአቅራቢዎች ወርቅ በመግዛት እንዲሁም የጂኦሎጂካል ሰርቬይ ማዕቤት የወርቁን ጥራት እና ክብደት መርምሮ በሚያገግጥ ሁለቱ ድርጅቶች በጋራ ሥራውን ያከናውናሉ፡ የሥራ ሂደቱም እንደሚከተለው ይሆናል፣

4.1 አቅራቢዎች/ነጋዴዎች ወርቁን ለመሸጥ ወደ ባንኩ በግንባር መቅረብ ይኖርባቸዋል፣

4.2 ወርቁን ይዞ የመጣው ሰው የተመዘገበ አቅራቢ መሆኑ ከግል ማህደሩ የቮልት ኃላፊዎች ያረጋግጣሉ፡ አቅራቢው አዲስ ከሆነና ያልተሟላ ሰነድ ካለ ግን በተራ ቁጥር 3 ላይ በተጠቀሰው መሠረት ሰነዶቹ እና ማስረጃዎቹ በጥንቃቄ እንዲሟሉ ይደረጋል፣

4.3 የወርቅ ግዥ ኃላፊዎች ወርቅ መቅረቡን እንዳወቁ ከጂኦሎጂካል ሰርቬይ ባለሙያዎች ጋር በመሆን ወርቁን ይረከባሉ፣

4.4 የጂኦሎጂካል ሰርቬይ ባለሙያዎች የወርቁን መጠን እና ጥራት ለሚያገግጥ ምርመራውን ያካሂዳሉ፣

4.5 የቀረበው ወርቅ አቅራቢው ወይም ወኪሉ ባሉበት፣ የወርቅ ግዥ ኃላፊዎች እና የውስጥ ቁጥጥር ሠራተኛ በተገኙበት ወርቁ በጂኦሎጂካል ሰርቬይ ባለሙያዎች የጥራት ደረጃውና የክብደት መጠኑ ይረጋገጣል፣

4.6 የጂኦሎጂካል ሰርቬይ ባለሙያዎች የወርቁን ጥራት በካራት እንዲሁም ክብደቱን በግራም በማመልከት ሕጋዊ የጥራት እና የክብደት ሚያገግጫ ሰርተፊኬት በ6 ኮፒዎች አዘጋጅተውና ፈርመው አንዱን ለአቅራቢው፣ አንድ ኮፒ ለብሔራዊ ባንክ፣ አንዱ ከወርቁ ጋር በሳጥን ውስጥ የሚቀመጥ ሆኖ ወርቁ በግዥ ማዕከላት በኩል ከተፈጸመ አንድ ኮፒ ለቅርንጫፍ ንግድ ባንክ የተቀሩትን ራሳቸው ይይዛሉ፡ የንግድ ባንክ ቅርንጫፍ የወርቅ ግዥ ኃላፊዎች የዚህን ሰርተፊኬት አንድ ኮፒ ወርቁን ለብሔራዊ ባንክ ሲያስረክቡ አብረው አያይዘው ያቀርባሉ፣

4.7 ለአቅራቢዎች ክፍያ እስኪፈጸም ድረስ ማጣሚቸ እንዲሆን የግዥ ማዕከላት ለወርቅ አቅራቢዎች ሰርተፊኬት አዘጋጅተው ይሰጣሉ፡፡ ግዥው በንግድ ባንክ የተፈጸመ ከሆነ የሰርተፊኬቱን አንድ ኮፒ ለብሔራዊ ባንክ ይልካሉ፣

4.8 የወርቁ ምርመራ ተከናውኖ ከላይ የተጠቀሱት ሰነዶች ተሟልተው ለሚመለከታቸው እንደተሰጡ ወርቁ ከአንድ ኮፒ የአቅራቢዎች ሰርተፊኬት ጋር እና ከጥራት ማረጋገጫ ሰነድ ጋር ተደርጎ በሳጥን ውስጥ ተከቶ ዙሪያው ይታሸጋል፡፡ ይህ ተግባር ከተደረገ በኋላ ተረካቢዎች እና የውስጥ ቁጥጥር ሠራተኛ በታሸገው ሳጥን ላይ ፈርመው በቮልት እንዲቀመጥ ተደርጎ ይቆለፍበታል፡፡ ክልል በሚገኘው የወርቅ ግዥ ማዕከላት የሚገዛው ወርቅ በቮልት ኃላፊዎች እና በጂኦሎጂካል ሰርቬይ ባለሙያዎች ቁጥጥር ሥር ይቆያል፡፡

4.9 ብሔራዊ ባንክ በሚገኘው የግዥ ማዕከል የሚገዛው ወርቅ የሚቀመጥበት ቮልት ቁልፍ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወርቅ ቮልት ኃላፊዎች በጋራ ይይዛሉ፡

4.10 የተገዛውን ወርቅ እና የተከፈለውን ገንዘብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በዕለቱ የሂሳብ ማዛኪያ ሥራ ይከናወናል፡፡ ይህም በየዕለቱ በኦዲተር ተፈርሞ ይረጋገጣል፡፡

4.11 ብሔራዊ ባንክ የሚገኘው የወርቅ ግዥ ማዕከል እና የንግድ ባንክ ቅርንጫፎች የሚገዙት ወርቅ ክብደቱ 50 ግራም እና ከዛ በላይ ሆኖ፣ የጥራት ደረጃው 14 ካራት እና ከዛ በላይ መሆን አለበት፡፡

5. የወርቅ ግዥ የክፍያ አፈጻጸም ሥርዓት

5.1 ማንኛውም አቅራቢ ባንኩ የሰጠውን ማበረታቻ ለመጠቀም በማሰብ እስከ 30 ቀናት ድረስ ዋጋው በዋጋው ያልተከፈለ ወርቅ ማስቀመጥ ይችላል፡፡ አቅራቢዎች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ክፍያ ማጠየቅ ከፈለጉ የወርቁን ዋጋ 95% ብቻ በቅድሚያ እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡ የወርቁ ዋጋው ክፍያ አቅራቢያዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5.6 በተገለጸው መሰረት ይፈጸማል፣

5.2 የተፈቀደው የወርቅ ማስቀመጫ ጊዜ የሚያበቃበት ቀን በሳምንቱ የእረፍት ቀናት ወይም በዓል ቀን ከሆነ የሚቀጥለው የሥራ ቀን ወርቅ አቅራቢው ዋጋውን የሚመርጥበት እና ክፍያውን የሚጠይቅበት ሆኖ የወርቁ ዋጋ ይታሰባል፣

5.3 ደንበኛው ባቀረበው የክፍያ ማጠየቂያ ደብዳቤ መሠረት በፋይል ተይዘው የሚገኙ መረጃዎች ማለትም የጥራት ማረጋገጫ ሰነድ፣ የወርቅ አቅራቢዎች ሰርተፊኬት Sales Certificate ዝርዝር መረጃዎች ጋር በማመሳከር ለዚሁ የተመደቡ ሠራተኞች የክፍያ ሂሳብ ስሌቱን እንዲያዘጋጁ ይደረጋል፣

5.4 በብሔራዊ ባንክ ዋናው ማኀቤት እና በቅርንጫፍ ንግድ ባንኮች የሚደረገው የወርቅ ግዥ ቀጥሎ የተጠቀሱትን የዋጋ ማበረታቻ ምድቦች (price incentive categories) መሰረት በማድረግ ለአቅራቢዎች ክፍያ ይፈጸማል፡-

- 5.4.1. የአቅርቦት መጠኑ ከ50 ግራም እስከ 150 ግራም በአለም አቀፍ የወርቅ ዋጋ ላይ 10% ጭማሪ በማድረግ፣
- 5.4.2. የአቅርቦት መጠኑ ከ151 ግራም እስከ 1ኪሎ ግራም በአለም አቀፍ የወርቅ ዋጋ ላይ 25% ጭማሪ በማድረግ፣
- 5.4.3. የአቅርቦት መጠኑ ከ1.1 ኪሎ ግራም እስከ 5 ኪሎ ግራም በአለም አቀፍ የወርቅ ዋጋ ላይ 27% ጭማሪ የሚደረግ፣ እና
- 5.4.4. የአቅርቦት መጠኑ ከ5 ኪሎ ግራም በላይ በአለም አቀፍ የወርቅ ዋጋ ላይ 29% ጭማሪ ተደርጎ ግዥው ይፈጸማል፡፡

5.5 ወርቅ አቅራቢ ማህበራትን/ግለሰብ ነጋዴዎችን ለማበረታታት ታስቦ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባስቀመጠው አሠራር መሠረት አቅራቢዎች ወርቁን በባንኩ ማዕከላዊ የወርቅ ግዥ ቢሮ ወይም ክልል ለሚገኙ የግዥ

ቅርንጫፎች ካስረከበበት ቀን ጀምሮ ክፍያ መጠየቅ ይቻላሉ፡ ማንኛውም ወርቅ አቅራቢ ለሚቀርበው ወርቅ ሽያጩ እንደተፈጸመ ሙሉ በሙሉ (100%) ክፍያ የሚፈልግ ከሆነ በዕለቱ የዋለው አለም አቀፍ የወርቅ ዋጋ ላይ በአንቀጽ 5.4 ከተጠቀሱት መካከል አግባብ ካለው የማበረታቻ ተመን ጋር ተደምሮ እና በቀረበው ወርቅ መጠን ተባዝቶ ክፊያ ይፈጸማል፡፡ በዚህ መልክ የተደረገ ሽያጭ በአንድ ጊዜ የሚፈጸም በመሆኑ በምድቡ ከተሰጠው የማበረታቻ ተመን ባለፈ ሌላ የማበረታቻ እርከን አይኖረውም፡

5.6 አቅራቢው ድርጅት/ግለሰብ ነጋዴዎች ለሚቀርቡት ወርቅ ከእያንዳንዱ ሽያጭ 95% በመውሰድ ወርቁን ባስረከቡ በ30 ቀናት ወይም ከዚያ ባነሰ ጊዜ በተከታታይ ያቀረቡት ወርቅ ተደምሮ ክፍያ እንዲፈጸምላቸው የሚፈልጉ ከሆነ ወርቅን ለባንኩ አቀርበው ሽያጭ ከፈጸሙበት ዓለም አቀፍ የወርቅ ዋጋ ተመኖች መካከል ከፍተኛውን ዋጋ በመውሰድ እና በአንቀጽ 5.4 ከተገለጹት የማበረታቻ ተመኖች አግባብ ካለው ጋር ተደምሮ የተገኘው ውጤቱ ባቀረቡት ወርቅ ጠቅላላ መጠን ተባዝቶ ዋጋ ከታወቀ በኋላ ቅድሚያ ክፍያው ተቀንሶ እና ቀሪው 5% ተደምሮ ክፍያው ይፈጸማል፡፡

5.7 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወርቅ ለሚገዙ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች በየዕለቱ የወርቅ ዋጋ ተመን እያዘጋጀ ይልካል፡፡ የወርቅ ዋጋ ስሌት ከባንኩ በሚላከው ተመን ብቻ ይከናወናል፡፡

5.8 የስሌቱ ትክክለኛነት በውስጥ ቁጥጥር ሠራተኛ/ኦዲተር ከተረጋገጠ በኋላ በወርቅ ግዥ/ኃላፊዎች ተፈርሞ ክፍያው ለአቅራቢው በሂሳቡ ገቢ ይደረጋል፣

5.9 ንግድ ባንክ እና ብሔራዊ ባንክ ለወርቅ አቅራቢዎች ለሰጡት አገልግሎት ከቀረበው የወርቅ ዋጋ /ከአቅራቢው/ **0.1%** ቀንሰው ለራሳቸው ገቢ ያደርጋሉ፡

6. <u>የሂሳብ አመዘጋገብ ሥርዓት</u>

በማንቸውም ጊዜ የንግድ ባንክ ቅርንጫፍ እና ብሔራዊ ባንክ ለገዙት ወርቅ ክፍያ እንደፈጸመ በእለቱ ተገቢውን ሒሳብ በኮምፒተር ሲስተም ላይ ያሰልፉሉ፡ በዚሁ መሠረት፣ በንግድ ባንክ የግዥ ማዕከላት የሚገዛውን ወርቅ በሚመለከት ሁለቱ ባንኮች በየራሳቸው እንደሚከተለው ይመዘግባሉ፡

6.1. ብሔራዊ ባንክ ወርቅ የሚገዛበትን ገንዘብ ወደ ንግድ ባንክ ሲያስተላልፍ /በብሔራዊ ባንክ የሚሠራ/

Dr. Advance for Gold Purchase

Cr. CBE Payment and Settlement Account

6.2 ገንዘቡ ወደ ቅርንጫፍ ባንኮች ሲተላለፍ / (CBE- at the center)

Dr. NBE - Mirror Account (CBE)

Cr. Enter Branch Account (CBE)

6.3. በንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ላይ የሚሰራ የሂሳብ ሥራ

Dr. Enter Branch Account (CBE)

Cr. NBE Gold deposit Account (at branch)

6.4. ገንዘቡ ለወርቅ አቅራቢዎች ሲከፈል (CBE)

Dr. NBE Gold Deposit Account (Branch)

Cr. Customer Account

Cr. Service Charge – CBE

Cr. Gold held for NBE - (Contingent Liability Account)

6.5. ንግድ ባንክ ወርቁን ለብሔራዊ ባንክ ሲያስረክብ (NBE)

Dr. Gold Commodity Account

Cr. Advance for Gold Purchase – CBE Branches

6.6 ንግድ ባንክ ወርቁን ለብሔራዊ ባንክ አስረክቦ ከብሔራዊ ባንክ ሚያገጫሲያገኝ በንግድ ባንክ የሚሠራ፣

Dr. Gold held for NBE (Contingent Liability Account)

6.7 ብሔራዊ ባንክ ከወርቅ አቅራቢዎች በማዕከል ሲገዛ፣

Dr. Gold Commodity Account

Cr. Payments and Settlement account-CBE Customer account

7. <u>ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወኪል ቅርንጫፎች ወርቅ የማጓጓዝ ሂደት</u>

7.1 ወርቅ ከሀዋሳ በስተቀር ከሌሎች የንግድ ባንክ ቅርንጫፎች ሲጓጓዝ በፌደራል ፖሊስ አባላት ታጅቦ አይሮኘላን ሚፈያ ደረስ ይጓጓዛል፡፡ ይህንንም የወርቅ ግዥ ማዕከሉ ይፈጸማል፣

7.2 ሀዋሳን በተማከተ የተገዛወዓ ወርቅ በዝግ መኪና/Van በፌደራል ፖሊስ ታጅቦ ይጓጓዛል፡፡ ትራንስፖርቱን በተማከተ የወርቅ ግዥ ማዕከሉ ያማቻል፡፡ ከሌሎች ግዥ ማዕከላት የሚጓጓዘወዓ ወርቅ በአይሮፕላን ማጓጓወን ካልተቻለ ባንኩ በሚወስነው መሰረት በመኪና ለጓጓዝ ይችላል፣

7.3 የኢንሹራንስ እና የትራንስፖርት ወጪ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይሸፈናል፡፡

8. <u>ከንግድ ባንክ ቅርንጫፎች ወርቅ የሚከብ ሂደት</u>

8.1 ሁሉም የንግድ ባንክ ቅርንጫፎች የገዙትን ወርቅ በየሁለት ወሩ ለብሔራዊ ባንክ ያስረክባሉ፡፡ ወይም የተገዛው ወርቅ መጠን ዝቅተኛ ከሆነ ርክክቡ በብሔራዊ ባንክ ታይቶ የሚወሰን ይሆናል፡፡ የርክክቡም ሂደት እንደሚከተለው ይሆናል፣

8.1.1 በየዕለቱ እየተገዛ በቮልት የተከማቸወዓ እና በሳጥን የታሸገወዓ ወርቅ በቀን ቅደም ተከተል እና በሳጥን ቁጥር በማስጠት ያዘጋጃሉ፣

8.1.2 በተራ ቁጥር 10 ከተጠቀሰው ሪፖርት ጋር በጊዜ ገደቡ ከተገዛው ወርቅ ጋር በሚደረግ በወርቅ ግዥ ኃላፊ በተፈረመ ደብዳቤ ሽኝነት ለብሔራዊ ባንክ ይላካል፣ ወርቁንም ግዥወዓ የፈጸመው የጂኦሎጂካል ሰርቬይ ባለሙ ከንግድ ባንክ የወርቅ ግዥ ኃላፊ/ባለሙ ጋር በመሆን ያስረክባሉ፣

8.1.3 ከንግድ ባንክ ቅርንጫፎች የተላከው ወርቅ ተያይዞ ከቀረበው ሪፖርት ጋር ተማክሮ እና በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ባለሙዎች የጥራት ደረጃው እና መጠኑ ተረጋግጦ በብሔራዊ ባንክ የወርቅ ግዥ የቮልት ኃላፊዎች ርክክቡ ይፈጸማል፡፡ የርክክብ ሰነደም ተፈርሞ አንድ ኮፒ ወርቁን ይዘው ለሚመጡ ሁለት ኮፒ ለከረንሲ ሜጀመንት ሌላወዓ ኮፒ ክፍሉ ይይዛል፡፡

9. በቅርንጫፍ ወኪል ባንኮች የተገዛው ወርቅ መጠን ወይም ካራት በማዕከል በሚደረገው ማጣራት ወቅት የሚታየው ልዩነት ከጣያው አኳያ ታይቶ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ከሚያወጣው ስታንዳርድ በተለየ ሜከ ከፍ ብሎ ከተመዘገበ የጥራት/ክብደት ደረጃወዓ የለካው ባለሙ ኃላፊነቱን ይወስዳል፡፡

10. <u>የሪፖርት አቀራረብ ሥርዓት</u>

በክልል የወርቅ ግዥ ወኪል ቅርንጫፍ ባንኮች በየጊዜው የገዙትንና ያጠራቀሙትን ወርቅ፣ በሻጭ ድርጅት/ግለሰብ ስም፣ በጥፍጥፍ (Bar)፣ በወርቁ መጠን /ክብደት፣ ጥራት እና የተከፈለወዓ ገንዘብ 100%፣ 95% ወይም 5% ተጠቅሶ ሪፖርት በብር በየሳምንቱ ዓርብ ጠዋት ለከረንሲ ሜጀመንት ዳይሬክቶሬት ይልካሉ፡፡ የአራተኛው ሳምንት ሪፖርት ጠቅላላ የወሩን ግዥ ይይዛል፡፡

11. የሰነድ አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት

11.1 እያንዳንዱ ወርቅ አቅራቢ በስሙ የተያዘ ማህደር ይኖረዋል፡፡ በማህደሩ ውስጥ በቁጥር 3 ከተራ ቁጥር 3.1 - 3.7 ላይ የተጠቀሱ ሰነዶች እና በየጊዜው የወርቅ ግብይት የተደረገባቸው 5 ኮፒ ሰነዶች እና ሁለት የሪፖርት ፎርሞች ማለትም፣

1. የጥራት ማረጋገጫ ሰነዶች /በእያንዳንዱ ግዥ/፣
2. የወርቅ ግዥ ሠርተፊኬቶች /በእያንዳንዱ ግዥ/፣
3. ክፍያዎች የተጠየቁበት ደብዳቤዎች /በእያንዳንዱ ግዥ/፣
4. እያንዳንዱ ክፍያ የተሰላበት ሰነድ (Calculation Sheet) /ለእያንዳንዱ ግዥ/፣
5. ለእያንዳንዱ ግዥ የክፍያ ትዕዛዝ የተሰጠበት ሰነድ በአንድነት ይያያዛሉ፣
6. ሳምንታዊ እና ወርሃዊ የሪፖርት ፎርሞች፡፡

11.2 የሰነዶቹ ዝርዝር (Index) ተጽፎ ከማህደሩ ጋር ተያይዞ ሰነዶቹን በፊደል ቅደም ተከተል ለማየት በሚያስችል ሁኔታ ከፋይሉ ጋር ተያይዘው በፋይል ካቢኔት ውስጥ ከላይ በተጠቀሰው ሜለክ ተደራጅተው በማዕከል ደረጃ የወርቅ ግዥ ኃላፊዎች (ፀሐፊ) ክፍል ቁጥጥር ሥር ተቆልፎባቸው የሚቀመጡ ሲሆን፣ ሚሂጃ ሲፈለግ በኃላፊዎች ብቻ እንዲወጡ ይደረጋል፣

11.3 የብሔራዊ ባንክ ማዕከላዊ የወርቅ ግዥ ቢሮ እና ክልል የሚኙ የግዥ ማዕከላት በየዓመቱ ወይም የክልሎችን የፈቃድ ዕደሳት ጊዜ መሰረት ባደረገ ሜለኩ በተወሰነ የጊዜ ገደብ የታደሰ የወርቅ ፈቃድ በፋይል ይይዛሉ፡ ኮፒውን ለብሔራዊ ባንክ ይልካሉ፡

12. የሥራ ሂደቱ መመሪያ ተፈጻሚነት

ይህ የወርቅ ግዥ፡ አጠባበቅና ማጓጓዝ አፈጻጸም የውስጥ አሠራር የሥራ ሂደት መመሪያ ከመጋቢት 24፣ 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ስለ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ	ስለ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
ስም --	ስም ------------------
ፊርማ ----------------------------------	ፊርማ ----------------------
ቀን 24/07/12	ቀን 24/07/12

Form I

ID.No.------

GEOSCIENCE LABORATORY CENTER

LABORATORY RESULTS REPORT FORMAT

FOR GOLD KARAT DETERMAINATION

Signator:______________________________ File Name: GBKNBE__________________

Approved by: Head C.G.L

Preparation Required: None Date Received :_____________(--/--/--)

Area Reference: _______________ Sample Type: Gold Bar

Analytical Method: Specific Gravity Method (densitometry)

Job Title: Name___________________ GBK NBE No. _________________ Gold Karat Determination

ANILYTICAL RESULTS

Supplier No.	Lab. No	Wt. Of Au bar in grams	Specific gravity	Purity of Au in Karat	Purity of Au in percent (%)	Fineness (%)
	GBKNBE---/---					
	GBKNBE---/---					
TOTAL WEIGHT						

Confirm that the above — Gold Bars are analyzed by specific gravity method and above results are given to the concerned bodies.

Alanis : Checked by

Completed: -------------------------------------
Certificate is Issued:

1 Original for the Supplier

3 Copies for National Bank of Ethiopia

1 Copy for file

1 Copy to be enclosed with Gold Bar (s)

1 Copy for chemical Lab.

1 Copy for office of Ministry of Mines

Form 2

ሴሪ ቁጥር

የወርቅ አቅራቢዎች ሰርተፊኬት

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ______________________________ ቅርንጫፍ

የወርቅ አስቀማጭ ስም ______________________________

የቀረበው የወርቅ ማጠን ክብደት በዝርዝር፡ ______________________________ ግራም

ጠቅላላ ክብደት ________________________ ግራም

የጥራት ደረጃውን ያረጋገጠው ድርጅት ስም የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ዋና ላቦራቶሪ___________ቅርንጫፍ

የሰርተፊኬት ቁጥር GBKCBE_________________/ወርቁ የቀረበበት ቀን ---------- እ.ኤ.አ.

የካራቱ ማጠን በዝርዝር ___________ እና ___________ካራት

የተፈቀደው የወርቅ ማስቀመጫ ጊዜ የሚያበቃበት ቀን----እ.ኤ.አ. ይህ ቀን በሥራ ቀን ካልዋለ በቀጣዩ የዋለው የሥራ ቀን የሚጨረሻ ይሆናል፡፡

ከላይ ከፍ ብሎ መጠኑ የተገለፀውን እና ጥራቱ በጂኦሎጂካል ሰርቬይ የተረጋገጠ ወርቅ ለባንኩ የሚያቀርብ ወርቅ አቅራቢ፣ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያቀረበው ወርቅ፣ (1) ወርቁን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ተከታታይ ቀናት ባለው ጊዜ ብቻ አቅራቢው በሚፈጠው ዋጋ ወስኖ እስከሚሸጥ ወርቁን ማስቀመጥ የሚችል ሲሆን፣ እስከዚያው ወርቁ ያወጣል ተብሎ የሚገመተውን ዋጋ 95% ያህል በቅድሚያ ክፍያ በአስገባበት ቀን ወይንም አስገቢው በጠየቀበት ቀን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የዓለም የወርቅ ገበያን ተመርኩዞ በሚያወጣው የወርቅ ገበያ ሰንጠረዥ መሠረት ማጠየቅና መውሰድ ይችላል፡፡ ቀሪውን 5% ክፍያና የተጣሩ ልዩነት ስሌት በ30 ተከታታይ ቀን ባለው በሚፈጠው ቀን በዋለው የዓለም ገበያ መሠረት መውሰድ ይችላል፡፡ ይንን አሠራር አቅራቢው ተገንዝቦ ስምምነት ገብቷል፡፡ በዚሁ መሠረት፣ አቅራቢው ከፍ ብሎ በተገለፀው የ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለባንኩ ያቀረበውን ወርቅ ዋጋውን ወስኖ ካልሸጠ፣ ባንኩ የቀረበውን የወርቅ ዋጋ ወርቅ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ሰላሳኛው ቀን ከዋለበት ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን በሚወጣው የዓለም የወርቅ ዋጋ ስሌት መሰረት ተሰርቶ የተረከበውን ወርቅ ዋጋ በመክፈል ሙሉ በሙሉ በመግዛት የራሱ ንብረት ያደርጋል፡፡ (2) ወርቁን ለ30 ተከታታይ ቀናት እላይ በተገለፀው መሠረት እንዲሆን ካልፈለገ ባቀረበበት ቀን ባለው የዓለም ገበያ ዋጋ መሠረት ላይ ተመስርቶ ሙሉ በሙሉ 100% ክፍያውን ጠይቆ መውሰድ ይችላል፡፡ የክፍያ ማጠየቂያ ደብዳቤ ማቅረቢያ ቀን ወስነው ከፃፉና ዋጋ ከቆረጡ በኃላ መቀየር አይቻልም፣ እንዲሁም የማጠየቂያው ደብዳቤ ዋና ክፍሉ በደረሰበት ቀን ይመዘገባል፡፡

በአቅራቢው ተጠይቆ የሚከፈለው ሙሉ ክፍያም ሆነ ለአቅራቢው የተሰጠው የ30 ቀናት የዋጋ መወሰኛ አማራጭ ጊዜ ካበቃ በኋላ በባንኩ የሚፈፀም ክፍያ እንደሚጨረሻ ግዥና ሽያጭ የሚቆጠር ሲሆን የወርቅ የባለቤትነት መብትም ወዲያውኑ ወደ ባንኩ ይዞራል፡፡

በተሰጠው የ30 ቀናት የመሸጫ ዋጋ ማምረጫ ጊዜ ውስጥ የተሻለ የመሸጫ ዋጋ ለባንኩ በሚቀርብበት ጊዜ ወይም የ100% የሙሉ ክፍያ ጥያቄ በአቅራቢው በተረጋገጠ የጽሁፍ ጥያቄ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

	ፊርማ	ቀን
1. አቅራቢ (ሻያጭ)	________________	____________ እ.ኤ.አ.
2. ተረካቢ (ገዥ)		
2.1	________________	____________ እ.ኤ.አ
2.2	________________	____________ እ.ኤ.አ.
3. ያረጋገጠው የውስጥ ቁጥጥር ሠራተኛ	________________	________________
4. ታዛቢዎች		
4.1	________________	____________ እ.ኤ.አ
4.2	________________	____________ እ.ኤ.አ

ይህ ሰርተፍኬት በአምስት ኮፒዎች የሚዘጋጅ ሆኖ አንደኛው ለአቅራቢው (ሻጭ) የሚሰጥ፣ አንዱ ለታዛቢዎች ሲሆን ቀሪዎቹ ሦስት ኮፒዎች በተረካቢው (ገዥ) እጅ ይቀመጣሉ፡፡ ይህ ሰርተፊኬት እንደ ቃለ-ጉባኤ ጭምር ይቆጠራል፡፡ በጊዜ ገደብ ተወስኖ ክፍያው የሚፈፀምበት የሽያጭና የግዥ ውል ነው፡

Form 5

Serial No-----------

GOLD PAYMENT WORKSHEET

1. Supplier’s name
2. Account holder
3. Account number
5. Application received
6. Date chosen
7. Deadline
8. Gold received on

Morning fix of London Metal Exchange Market
Selling/Buying price of Gold as of the date Chosen By the
Supplier for 1st payment (Rate)

				Gold Supplied		
No.	Karat A	Price per gram B			Karat C	Converted Price D=(C*B)/A
Gold supplied						
Karat F	Weight in Gram E		Price Per Gram G			Total price 100 % H=E*G
Total						
Commission: Net pay *0.1%						
Net pay after dedication-------------------------------------						0.00

Name _________________________ Signature: ___________________

Prepared by: ___________________ ___________________

Checked by: ___________________ ___________________

Prepared by dually:_________________

Form 4

Serial No-----------

GOLD PAYMENT WORKSHEET

1. Supplier’s name
2. Account holder
3. Account number
4. Gold received on
5. Application received
6. Date chosen
7. Deadline

8. Morning fix of London Metal Exchange Market Selling / Buying price of Gold as of the date Chosen By the supplier for the second payment (Rate)				Gold Supplied	
No.	Karat A	Price gram B		Karat C	Converted price D=(C*B)/A
Gold Supplied		Price per gram G	Total Price, 100 % H=E*G		Net pay,95% Of total price I=H-J
Karat F	Weight in gram E				
Total					
Commission (Net pay)*0.1 %					
Net pay after dedication------------------------					0.00

Name:___________________________ Signature___________________

Prepared by:__________________ ___________________

Checked by:__________________ ___________________

Prepared by dually:__________________

Form 3

Serial No-----------

GOLD PAYMENT WORKSHEET

1. Supplier's name
2. Account holder
3. Account number
4. Gold received on
5. Application received
6. Date chosen
7. Deadline

8.Morning fix of London Metal Exchange Market Selling / Buying price of Gold as of the date Chosen By the supplier for Second payment (Rate)			Supplied gold	
No.	Karat K	Price per gram (in Birr) L	Karat M	Converted Price N=(M*L)/K

No	Supplied gold		Price per gram (from N) Q	100% of 2^{nd} price, R=P*Q
	Karat O	Weight in gram P		
	0.00			0.00

% of 1^{st} payment From: J: S	100 % of 1^{st} price S*10 T=S*10	100 % of 2^{nd} price (From R) U	Net 2^{nd} pay V=S+(U-T)	Total paid (1^{st} payment+2^{nd} payment) w=s*9+v
				0.00

Commission: Net pay *0.1%	
Net pay after dedication: ---------------------------------	

Note: Total payment should not exceed from 100 % of 2^{nd} price i.e , W<U

Name: ______________________ Signature: __________________

Prepared by:__________________ __________________

Checked by:__________________ __________________

Prepared by dually:_____________

FORMAT NO.6

COMMERCIAL BANK OF ETHIOPIA

--------------------------------BRANCH

MONTHLY GOLD PURCHASE REPORT

WITH IN THE DATE OF--------------------

DATE OF PURCHASE	SUPPLIER NAME	NO.OF BAR	WEIGHT IN AIR	WEIGHT IN WATER	SPECIVICE GRAVITY	KARAT	APPLICATION DATE	DATE OF PAYMENT	100 % PAYMENT IN BIRR
TOTAL									

BEGINNING BALANCE OF THIS WEEK	BIRR
AMOUNT CREDITED TO NBE GOLD PURCHASE ACCOUNT	BIRR
100% PAYMENT MADE	BIRR
ENDING BALACE OF THIS WEEK	BIRR

Audited By: -------------------------

Signature: -----------------------------

FORMA NO.7

COMMERCIAL BANK OF ETHIOPIA

--------------------------------BRANCH

WEKKLY GOLD PURCHASE REPORT

WITH IN THE DATE OF--------------------

DATE OF PURCHASE	SUPPLIER NAME	NO.OF BAR	WEIGHT IN AIR	WEIGHT IN WATER	SPECIVICE GRAVITY	KARAT	APPLICATION DATE	DATE OF PAYMENT	100 % PAYMENT IN BIRR
TOTAL									

BEGINNING BALANCE OF THIS WEEK	BIRR
AMOUNT CREDITED TO NBE GOLD PURCHASE ACCOUNT	BIRR
100% PAYMENT MADE	BIRR
ENDING BALACE OF THIS WEEK	BIRR

Prepared By:- ---------------------------------------

Audited By: -------------------------

Signature: -----------------------------